# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅ ሠነዶች፡-** DIA-RB፣ DJA፣ DJA-RB
**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፡-** የፋይናንስ ዋና ኃላፊ ቢሮ
Office of the Chief Financial Officer

## የሥራ መሳሪያዎች፣ ትጥቆች፣ የግብአት፣ እና የአገልግሎቶች ግዥ

I. **አላማ**

ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ የተወሰኑ እቃዎችን ለመግዛት ጨረታ ስለማውጣት፣ የኮንትራት አፈጻፀም ሂደቶችን ለመደንገግ፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚጠቀሙባቸውን የሥራ መሳሪያዎች፣ እቃዎች፣ እና አገልግሎቶችን ግዥ የመፈፀም ሃላፊነት እና አሰራር ለመደንገግ።

II. **ትርጉም**

A. የማይንቀሳቀሱ መሳሪያዎች ማለት ከህንፃው ጋር ተያይዘው የተሠሩ እና በመሬት ላይ የተገነቡ መሳሪያዎች ናቸው።

1. ከህንፃው ጋር ተያይዘው የተገነቡ መሳሪያዎች የሕንፃው አካል የሆኑ ቁሳቁሶችን የሚመለከት ነው። ይህ ማለት፥ መሳሪያዎቹ በህንፃው ላይ በቋሚነት ተጣብቀው የተሠሩ እና የሕንፃው አካል ሆነው የተገነቡ ሲሆን፥ ከተወገዱ በህንፃው ላይ ጉልህ የሆነ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። ለምሳሌ፡- የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ ቆጣሪዎች፣ የቅርጫት ኳስ ሰሌዳዎች፣ መደርደሪያዎች፣ ከመድረክ ጋር ተያይዘው የተሠሩ መጋረጃዎች፣ እና ከህንጻው አገልግሎት ጋር ተያይዘው የተሠሩ አየር ማቀዝቀዣዎች፣ የሙቀት እና የሙብራት አገልግሎት የሚሰጡ መስመሮች፣ የመገናኛ ኬብል መስመሮች እና የተዘረጉ የውሃ መስመሮች ናቸው።

2. በመሬት ላይ የተገነቡ መሳሪያዎች ማለት በመሬት ውስጥም ሆነ ከላይ የተዘረጉ መሳሪያዎች በመሆናቸው በቋሚነት ከመሬት ጋር ተያይዘው አገልግሎት ለመስጠት የተገጠሙ ናቸው። ምሳሌ፡- የባንዲራ ምሰሶዎች፣ በሮች፣ የግብ ምሰሶዎች፣ ከመሬት በታች ያለ የውኃ ጉርጓድ፣ ወይም የቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓድ፣ እና ሳር ላይ ውኃ ለመርጨት የተዘረጉ መስመሮች ናቸው።

B. የማስተማሪያ መሳሪያዎች ማለት፥ ትምህርት ለመስጠት ወይም ተማሪዎች ስርአተ ትምህርቱን በብቃት እንዲሠሩ ለማስቻል የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ያካትታል። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በምድብ 05 እንደ አላቂ እቃዎች ወጪ ይገልፃል።

C. የማስተማሪያ አቅርቦቶች የሚያካትቱት፥ ትምህርት ለማስተማር ወይም ተማሪዎች ስርአተ ትምህርቱን በብቃት ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን፣ የመማሪያ መጽሀፍትን፣ እና ሌሎች የሚዲያ መገልገያዎችን ይሆናል። MSDE የማስተማሪያ አቅርቦቶችን በምድብ 04 የወጪ መደብ ይገልፃል።

D. ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች ማለት፥ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማጓጓዝ የሚቻሉ ዕቃዎችን ማለትም ከተወገዱበት ቦታ ወይም ከተገጠሙበት ቦታ አንስቶ ጉልህ የሆነ ጉዳት ሳይደርስባቸው ወደ ሌላ ሥፍራ

የሚጓጓዙ ቁሳቁሶችን ያመለክታል። የህንጻው አካል ሆነው ከህንጻው ጋር ያልተያያዙ ወይም እንዳይንቀሳቀሱ ተደርጎ በግቢው መሬት ላይ ያልተዘረጉ እና በቋሚነት ከመሬት ጋር ተጣብቀው ያልተገነቡ ናቸው። "ተንቀሳቃሽ" የሚለው ቃል በቋሚነት ያልተገጠመ ተንቀሳቃሽ መሳሪያ መሆኑን እንጂ የእቃውን መጠን ወይም ክብደትን አይገልጽም። ለምሳሌ:- በወለል ላይ ወይም በግርግዳ ላይ በቀላሉ በመፍቻ የሚገጣጠም እቃ ለምሳሌ:- ክብደት ያለው የቅርፅ ማውጫ መሣሪያ ወይም የላቦራቶሪ ዴስክ የመሣሰሉ ብሎኖች ከተፈቱ ወይም ከተወገዱ በኋላ በቀላል ተንቀሳቃሽ እቃ ነው።

E. የፕሮግራም ኃላፊ ማለት ዋናው የአካዳሚክ ኦፊሰር፤ የትምህርት ቤቶች ድጋፍ እና ማሻሻል ምክትል ሱፐርኢንተንደንት፣ ዋና የሥራ አስፈፃሚ፣ እና የኮንትራት አገልግሎቶችን የመጠየቅ ስልጣን ያለው ማንኛውም የመምሪያ/የክፍል ዳይሬክተር ወይም ሌላ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የተሰየመ(ች) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ኃላፊነት ያለው አካል ነው።

F. የፕሮጀክት ማናጀር፥ ፕሮጀክቱን በይፋ በመወከል ከአገልግሎት ሰጪ ኮንትራክተር ጋር የመዋዋል እና የውሉን ቴክኒካዊ መስፈርቶች በተመለከተ በግዥ ጥያቄ እና ውል አፈጻፀም ላይ የተጠቀሰ(ች) ግለሰብ ማለት ነው።

G. አገልግሎቶች ማለት፥ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች አማካይነት አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ የፖሊሲ ቀረጻን፣ የውሳኔ አሰጣጥን፣ ወይም የቢዝነስ ማመልከቻዎችን የማከናወን፣ ሂደትን ለማካሄድ እንደ ባለሙያ የምክር አገልልጎት መስጠት የመሳሰሉ ሙያዊ አገልግሎቶችን ያካትታል። የአሰራር ስርዓቶችን ለማሣለጥ እና/ወይም አገልግሎቶችን ለማስቀጠል አገልግሎት ሰጪ ሊያስፈልግ ይችላል። በግምገማው ውጤት መሠረት የቴክኒካዊ እሳቤዎች እና የወጪዎች መመዘኛዎች ትክክለኛ ከሆኑ የተጠየቁትን አገልግሎቶች አቅርቦት ማግኘት ይቻላል።

## III. የአፈጻፀም ቅደም-ተከተሎች

A. የግዥ መመሪያው (ማኑዋሉ) ከመፅሃፍት እና ሌሎች የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በስተቀር ሁሉንም ለሥራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፣ የህግ አገልግሎት፣ የህንፃ አርኪቴክቸራል እና የምህንድስና አገልግሎቶች፣ ወይም የሕንፃዎች ግንባታ፣ መዋቅሮች፣ መሬት፣ ወይም ዋና የካፒታል መሳሪያዎችን መተካት፣ የመሣሰሉ አቅርቦቶች እና አገልግሎቶች ግዥዎችን የሚደነግግ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰነድ ነው። መመሪያው የዚህ ደንብ አካል ተደርጎ ይወሰዳል

1. የመመሪያውን ድንጋጌዎች ማሻሻል፣መጠበቅ፣ማሰራጨት እና የማስፈጸም ሀላፊነት የፋይናንስ መምሪያ ምክትል ኃላፊ ሥልጣን ነው።

2. መመሪያው የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ይሁንታን የሚሹ ግዥዎችን ገደብ በሙሉ ይዘረዝራል። $25,000 ዶላር እና ከዚያ በላይ የገንዘብ ወጪዎችን የሚያስከትሉ ግዥዎች በሙሉ ከጨረታ ውድድር በኋላ ቦርድ ማጽደቅ ይኖርበታል።

3. እንደ ፕሮግራም ኃላፊ ወይም የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሚሠራ ማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ በመመሪያው ውስጥ የተዘረዘሩትን የአፈጻፀም ሂደቶች የመከተል ሃላፊነት አለበ(ባ)ት።

B. የዳራ ማረጋገጫ መስፈርት እና የወሲብ ትንኮሳ የፈፀሙ ወንጀለኞችን የመቅጠር ክልከላ

1. በሜሪላንድ ህግ መሠረት፤ከተማሪዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ክትትል እና ቁጥጥር የማይደረግባቸው

ማንኛውም የሥራ ተቋራጭ ወይም የኮንትራክተር የስራ ባልደረባ የሆኑ ሁሉ የወንጀል ድርጊት ዳራ ማጣሪያ ምርመራ ማድረግ እና የጣት አሻራ መስጠት አለባቸው።

a. የኮንትራክተር የስራ ባልደረባ የሆነ(ች) ግለሰብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ቤት ተቋም ውስጥ ቀጥታ ክትትል እና ቁጥጥር ሳይኖር ከህጻናት ጋር መገናኘት በሚችልበት/በምትችልበት ሁኔታ ሥራ አይጀምርም/አትጀምርም።

i. የግለሰቡን(ቧ) የጀርባ ጥናት ውጤት ወደ MCPS ከደረሰ በኋላ

ii. MCPS ሰራተኞች ስልጠና ከሚወስዱት ኮርስ ይዘት ጋር በሚጣጣም ደረጃ ግለሰቡ(ቧ) የህጻናት ጥቃት እና ቸልተኝነትን ስለመገንዘብ፣ ሪፖርት ስለማድረግ፣ እና ስለመከላከል ስልጠና መውሰዱ(ዷ)ን እና/ወይም አግባነት ያላቸውን የመረጃ ቁሳቁሶች ማንበብ እና መረዳቱ(ቷ)ን በተመለከተ ኮንትራክተሩ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማረጋገጫ መስጠት አለበት፣ ከዚያ በኋላ

iii. ግለሰቡ(ቧ) MCPS መለያ ባጅ ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

2. ሥራ ተቋራጮች የወሲብ ጥቃት የፈፀመ(ች) ሪኮርድ ያለበትን ወንጀለኛ ገለሰብ እያወቁ በትምህርት ቤት ውስጥ ለማሠራት መቅጠር የለባቸውም።

a. እያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ የኮንትራት ውል ከተሰጠ በኋላ ቀጥተኛ ሰራተኞቹን እና የማንኛውንም ንዑስ የሥራ ተቋራጮች እና/ወይም ገለልተኛ ተቋራጮችን MCPS ትምህርት ቤት ተቋም ውስጥ ለኮንትራክተሩ ሥር እንዲሰሩ የተመደቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ ይጠበቅበታል።

b. በተጨማሪም ተቋራጩ ይህንን ግዴታ በየአመቱ እና/ወይንም ተቋራጩ እና/ወይም ንኡስ ተቋራጮቹ ውሉ ላይ የተዘረዘሩትን ስራዎች ለማከናወን በሚጠቀሙበት የሠራተኛ ሃይል ላይ ለውጦች ሲኖሩ ኮንትራክተሩ ይህንኑ ግዴታ በቀጣይነት መፈጸሙን ማረጋገጥ አለበት።

3. የእቃ ግዥ ክፍል በግዥ መመሪያው ላይ እንደተገለፀው ተገቢ የሆኑ ተጨማሪ የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን መቀየር/ማሻሻል ይችላል።

C. ኃላፊነት የሚመለከታቸው ባለስልጣናት

በተጨማሪ፣ከቦርዱ እና ተገቢ ሲሆን የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ሌላ በመመሪያው ውስጥ ለተገለጹት ልዩ ልዩ ተግባራት የሚከተሉት ኃላፊነት አለባቸው፦

1. የፕሮጀክት ማናጀሩ የኮንትራክተሩን አፈጻጸም ከገመገመ በኋላ ለኮንትራክተሩ ተገቢው ክፍያ እንዲፈፀም የክፍያ መጠየቂያዎችን ለአካውንት ኃላፊው ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች። የክፍያ ይሁንታ ያልተሰጣቸው ማናቸውም እቃዎች መመዝገብ አለባቸው።

2 የፋይናንስ ቢሮ ምክትል ኃላፊ የሚከተሉትን ጨምሮ የሥራ መሣሪያዎች ግዥ፣ አቅርቦቶች እና የአገልግሎት ግዥን በሚመለከት ለሁሉም የኮንትራት አስተዳደር ኃላፊነት አለበት።

a) ጨረታዎችን፣ የግዥ ጥያቄዎችን ማቅረብ፣ እና የውል ሰነዶችን መስጠት

b) ኮንትራት የመስጠት ፈቃድ ማግኘት

c) ኮንትራት መሰጠቱን ማሳወቅ

d) ክፍያዎችን መፍቀድ

e) የኮንትራት ውሎችን እና ሁኔታዎችን ማስፈጸም

f) አግባብነት ያላቸው ህጋዊ የውል ግምገማዎችን ማግኘት

3. የፋሲሊቲ ማኔጅመንት ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ የካፒታል ፕሮጀክቶችን፣ የመሬት ግዥዎችን፣ እና የሚከተሉትንም ጨምሮ የካፒታል ፕሮጀክቶችን ጨረታ እና ዋና ዋና የካፒታል ዕቃዎችን መተካት፣

a) የካፒታል ፕሮጀክቶችን ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑትን አርክቴክቶች፣መሐንዲሶች፣ የግንባታ ማኔጀሮች፣ እና ሌሎች ሙያዊ አገልግሎቶችን በብቃት ላይ የተመሰረተ የምርጫ ሂደቶችን ማካሄድ/መምራት

b) የበፊት ታሪካቸውን፣የኢንዱስትሪ ደረጃ እና የገበያ መረጃዎች ላይ በመመስረት ከፍተኛ ብቃት ካላቸው ድርጅቶች ጋር ክፍያዎችን መደራደር

c) ለተወሰኑ ፕሮጀክቶች የድርጅቶችን ቴክኒካዊ የብቃት መመዘኛ እና በጨረታ ያቀረቡትን ዋጋዎች ለመወሰን በአግባቡ የታሸጉ ጨረታዎች እንዲቀርቡ መጠየቅ።

d) ለካፒታል ፕሮጀክቶች ጨረታ ማውጣት፣ መደራደር፣ እና የኮንትራት ውል ሰነዶችን መስጠት

e) ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እና ለቦርድ ስለ ኮንትራት ተቋራጭ የውድድር አሸናፊ አስተያየት ማቅረብ

f) ሥራው እንዲቀጥል ኮንትራት መሰጠቱን ማሳወቅ

g) ክፍያዎችን መፍቀድ

h) የኮንትራት ውሎችን እና ሁኔታዎችን ማስፈጸም

4. የፋይናንስ ቢሮ በዚህ መመሪያ መሠረት በተለየ ሁኔታ የሚጠየቅ ተገቢ የገንዘብ ምንጮችን እና አፈጻፀሞችን ለመወሰን ለት/ቤቶች እና ቢሮዎች መመሪያዎችን ያዘጋጃል።

5. ትምህርት ቤቶች የትምህርት ክፍል እቃዎችን እና የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ግዥ በሚመለከት ለማስተማሪያ እቃ አቅርቦት የተያዘላቸውን ባጀት ለመጠቀም ከፋይናንስ ቢሮ ፈቃድ መጠየቅ አለባቸው።

6. የማስተማሪያ ኮምፒውተር ቴክኖሎጂን ለመግዛት የሚቀርቡ ጥያቄዎች በስትራቴጂክ ኢንሼቴቭ ጽ/ቤት ዋና ኃላፊ መጽደቅ አለባቸው።

***ተዛማጅ ሠነዶች፡***　　***የዕቃዎች ግዥ መመሪያ***

**የደንቡ ታሪክ፡** ማርች 26,1979 የቀድሞው ደንብ 235–1 በሥራ ላይ ዋለ፣ የመመሪያው ዝርዝር መረጃ ጃኑዋሪ 1983 ተሻሽሏል። ሜይ 2 ቀን 1988 ተሻሽሏል፣ ሴፕቴምበር 4, 1992 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 26 ቀን 2004 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ኖቬምበር 14 ቀን 2006 ተሻሽሏል፣ ዲሰምበር 12, 2011 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 1, 2013 ተሻሽሏል፣ ፌብሩዋሪ 1, 2016 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 20, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-

(1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

(a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣

(b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም

(c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጋንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024